የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.18
ADDIS ABABA , 20th May, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፫/፪ሺ፲፫

የፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር........................................ገጽ ፲፫ሺ፲፩

## Content

Proclamation No. 1233/2021

Federal Judicial Administration Proclamation..........................Page13011

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፫ /፪ሺ፲፫

## የፌደራል ዳኝነት አስተዳደር አዋጅ

በፍትህ አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛና ወሳኝ የሆነውን ሚና የሚጫወቱት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን ከማናቸውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው በገለልተኝነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን ያለባቸው በመሆኑ፤

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች ግልጽ፣ ገለልተኛና ተአማኒ በሆነ አሰራር የሚሾሙበትን ሥርዓት በመዘርጋት የፍርድ ቤቶችንና እና የዳኞችን ብቃት ፣ ነጻነት ፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዳኝነት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን ያስከበረ እና የሕዝብ አመኔታን ያገኘ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO.1233/2021

## FEDERAL JUDICIAL ADMINISTRATION PROCLAMATION

**RECOGNIZING** the vital role of courts in the administration of justice and the need to ensure that courts exercise their judicial functions free of all internal and external influences and in the spirit of complete independence and accountability;

**DETERMINED** to establish a judiciary that upholds the supremacy of the law and earns and maintains the trust of the people by ensuring transparency, impartiality and public confidence in the process by which judges are appointed as well as by ensuring that members of the judiciary conduct their judicial functions with complete independence, impartiality and accountability;

እነዚህን መሰረታዊ ዓላማዎች ለማሳካት አሁን ያለውን የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፬/፪ሺ፪ መሰረታዊ በሆነ መልኩ በማስተካከል በአዲስ አዋጅ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፫/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ጉባኤ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ነው፡፡

፪/ "ጽህፈት ቤት" ማለት የጉባዔው ጽ/ቤት ነው፡፡

፫/ "ሕገ መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፤

፬/ "ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ቤቶች" ማለት እንደ አግባብነቱ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ሁሉም ፌደራል ፍርድ ቤቶች ማለት ነው፤

**WHEREAS**, in order to achieve the above fundamental objectives, it is necessary to restructure the Judicial Administration Council established under Proclamation No.684/2010 in fundamental ways;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## CHAPTER ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Federal Judicial Administration Proclamation No.1233/2021".

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "**Council**" means the Federal Judicial Administration Council;

2/ "**Secretariat**" means the Secretariat of the Council;

3/ "**Constitution**" means the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

4/ "**Court or Courts**" means the Federal First Instance Court or the Federal Courts or the Federal Supreme Court or all Federal High Courts;

፭/ "ፕሬዚዳንት" ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ነው፣

፮/ "የጽህፈት ቤት ኃላፊ" ማለት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤትን እንዲመራ በጉባዔው የተሾመ ነዉ፡

፯/ "የፌደራል ዳኞች "ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾሙ ዳኞች ሲሆኑ ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንቶችን ይጨምራል ፡

፰/ "ደንብ" ማለት በጉባኤው የጸደቀ የዳኞች ሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት በጉባዔው የሚወጡ ደንቦችን ይጨምራል፣

፱/ "ረዳት ዳኛ" ማለት በሕግ ትምህርት ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ እና ዳኛ ሆኖ ሳይሾም ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ዳኞች ጋር ተመድቦ በተመደበበት ችሎት በዳኛ ቁጥጥር እየተደረገበት በዳኛ ሊሰሩ የሚገባቸው መሰረታዊ የሆኑ የዳኝነት ተግባራት ውስጥ ሳይገባ የዳኝነት ሥራን በማገዝ እንዲሰራ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሾመ ነው፣

፲/ "ኮሚቴ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በጉባዔው የተቋቋመ ኮሚቴ ማለት ነው፤

፲፩/ የኮሚቴ አባል" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ በጉባዔ የተቋቋመ ኮሚቴ አባል የሆነ ነዉ፡

5/ "**President**" means the President of the Federal Supreme Court;

6/ "**Head of Secretariat**" means a person appointed by the Council to lead the Secretariat of the Council;

7/ "**Federal Judge**" means any person who is appointed to work as a judge by the Ethiopia Federal Democratic Republic of House of Peoples Represenatives' including the Presidents and Vice-Presidents of the Federal Courts;

8/ "**Regulation**" means the Judicial Code of Conduct and Disciplinary Rules of Procedure approved by the Council and other Regulations enacted based on this Proclamation;

9/ "**Assistant Judge**" means a person who earns at least first degree in law and appointed by the council to carry out all judicial activities in support and under the supervision of a judge or judges except on basic judicial function of a judge;

10/ "**Committee**" means a committee established by the Council in accordance with Article 14 of this Proclamation;

11/ "**Committee member**" means a person who is a member of a Council assigned as member of a sub-committee established under Article 14 of this Proclamation;

፲፪/ "የአስተዳደር ሠራተኛ" ማለት ከዳኛ ውጭ የሆነን ማንኛውንም የፌደራል ፍርድ ቤት ተሿሚ እና ሌሎች የፍርድ ቤት ሠራተኛ ያጠቃልላል፤

፲፫/ "የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት" ማለት በዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ክስ ሥነ-ሥርዓት ደንብ የሥነ ምግባር ጥሰት መሆኑ የተመለከተ ማናቸውም ድርጊት ነው፤

፲፬/ "ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ" ማለት በዳኝነት ሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ የተመለከተ ድርጊት ሲሆን በዳኝነት ሥራ ላይ ሞያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች የሆነ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት መፈጸምን ይጨምራል፤

፲፭/ "ስመ ጥር ግለሰብ" ማለት በሞያዊ ብቃት፣ በሥነምግባር እና በአርዓያነት የተመሰገነ እና ማህበራዊ ተቀባይነት ከፍ ያለ፣ ለሕግ የበላይነት መከበር፣ ለማህበራዊ ፍትህ መስፈን እና በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ ለፍትህ ሥርዓት እድገትና ነጻነት መከበር የጎላ አስተዋጽኦ ያበረከተ ወይም ለማበርከት የሚችል ተብሎ የሚገመት ማለት ነው፤

፲፮/ "በዳኛ የሚከናወን መሠረታዊ የዳኝነት ሥራ" ማለት ችሎት ማስቻል፣ ፍሬ ነገሮችን እና አግባብነት ያለውን ሕግ መለየት፣ ጭብጥ መለየት፣ ጉዳዮችን ማስረከብ፣ አቤቱታ መስማት፣ ምስክር መስማት፣ ትዕዛዝ ፣ ብይን፣ ውሳኔ መስጠትና ማሰማት ማለት ነው፤

12/ "**Non-Judicial Staff**" means all personnel of the judiciary including personnel of the secretariat of Council other than appointed judges;

13/ "**Judicial misconduct**" means any act that is recognized as misconduct by the Regulation on the Judicial Code of Conduct and disciplinary rules of procedure;

14/ "**Manifest incompetence**" means an act which is specified in the Regulation on the judicial code of conduct and rules of disciplinary procedure and includes an act of committing error of law or fact unbecoming to the competence by training and experience which the profession requires;

15/ " **Distinguished individual** " means a person who, on account of her professional competence, integrity and commitment to supremacy of the law and social justice, has earned respect and acceptance and has contributed or would contribute to development of the justice system and supremacy of the law and social justice in Ethiopia;

16/ "**Basic Judicial Function of a judge**" means conduct hearings, identify material facts of the case and relevant applicable law, identify issues, receive testimony of witnesses, render and pronounce judgements, orders, hear applications of a party or parties;

፲፯/ **"ጊዜያዊ ዳኛ"** ማለት እንደማንኛውም የፌደራል ዳኛ መሰረታዊ የዳኝነት ስራን የሚሰራ፤ ለፌደራል ዳኝነት አካሉ የተቀመጡ ኃላፊነት እና ግዴታዎች ያሉበት ፤ በሙያውና በሥነምግባሩ ላቅ ያለ በጉባዔው ተመርጦ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለተወሰነ ጊዜ የሚሾም ሰው ማለት ነው፡

፲፰/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ የሰውነት ያለዉ አካል ነዉ፤

፲፱/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩/በፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዳኞች ግልጽ፣ ገለልተኛና ተአማኒ በሆነ አሰራር የሚሾሙበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በብቃት፣ በሙሉ ነጻነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት የሚያከናውኑበትን አሰራር ማረጋገጥ፤

፪/ የዳኝነት ሥርዓቱን ከማናቸውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖና ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ እንዲሰራ ማስቻል፤

፫/ የዳኝነት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን ያረጋገጠ፣ እንዲሁም የሕዝብ እርካታ እና አመኔታን ያገኘ እንዲሆን ማድረግ፡፡

## ፬. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በፌደራል ፍርድ ቤቶች፣ በማንኛውም ደረጃ በሚሾሙ የፌደራል ዳኞች፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የጉባዔ አባላት እና የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

17/ **"Ad-ohc Judge"** means Ad-hoc Judge is any person who is nominated by the council and appointed by the House of Peoples' Representative to serve as a Federal Judge for limited time in order to carry out basic judicial activities with the highest professional and ethical competence, and abides by the judicial responsibilities and duties;

18/**"Person"** means a natural or juridical person;

19/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Objective

This Proclamation shall have the following objectives;

1/ To establish a legal framework and procedures that ensure transparency impartiality and public confidence in the process by which judges are appointed as well as by ensuring that members of the judiciary conduct their judicial functions with complete independence, impartiality and accountability;

2/ To enable the judiciary to exercise its judicial function free from any and all internal and external influences;

3/ To maintain a Judicial System that upholds the supremacy of the law and earns and maintains satisfaction and trust of the people.

## 4. Scope Of Application

This Proclamation shall be applicable on Federal Courts and federal judges appointed at all level of Courts and non-judicial personal working in Federal Courts.

## ምዕራፍ ሁለት

## የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ስለማቋቋም

### ፭. መቋቋም

፩/ የፌደራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ጉባዔው በጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚመራ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ቋሚ ጽሕፈት ቤት እና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### ፮. የጉባዔው አባላት

፩/ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ) የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፤

ለ) የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ም/ፕሬዚዳንት፤

ሐ) የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤

መ) የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፤

ሠ) የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፤

ረ) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጡ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ሁለት የምክር ቤት አባሎች ፤

ሰ) በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጥ በዳኝነት ሥራ ቀደምትነት ያለዉ አንድ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፤

## CHAPTER TWO

## ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL JUDICIAL ADMINISTRATION COUNCIL

### 5. Establishment

1/ The Federal Judicial Administration Council (hereinafter referred to as “the Council”) is hereby established by this Proclamation.

2/ The Council shall have its own Secretariat Office with legal personality, head of Secretariat, budget and necessary staff.

### 6. Members of the Council

1. The Council shall have the following members:

a) The President of the Federal Supreme Court;

b) The Vice President of the Federal Supreme Court;

c) The Federal Attorney General;

d) The President of the Federal High Court;

e) The President of the Federal First Instance Court;

f) Two parialment members elected by the Federal House of Peoples Representatives which one female and one male;

g) A Senior Federal Supreme Court judge selected by all the Federal Supreme Court Judges;

ሸ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር፤

ቀ) ከሶስቱም ፌደራል ፍ/ቤቶች በዳኞች ጠቅላላ ስብሰባ የተመረጡ ሦስት ዳኞች፤ ከሶስቱ ሁለቱ ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡

በ) ከኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር ተመርጦ የተወከለ በጥብቅና ሥራ ከሰባት ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ያለው አንድ ጠበቃ፤

ተ) እውቅና ካላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች ማህበር ወይም የጋራ መድረክ ተመርጠው የተላኩ ከአስር ዓመት ያላነሰ የማስተማር አገልግሎት ያላቸው አንድ የሕግ መምህር፤

ቸ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፲፭ እና ጉባዔው በሚያወጣው መስፈርት መሠረት በጉባኤው ጠቅላላ ስብሰባ የሚመረጥ አንድ ስመ-ጥር ግለሰብ፤

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት እንደቅደም ተከተላቸው የጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

፫/ የጉባኤው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ኃላፊነቱን ለመወጣት በማይችልበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱ በሚወክለው አንድ የጉባዔው አባል የሆነ ዳኛ በጊዜያዊ ሰብሳቢነት በመሰየም ሥራው ሊከናወን ይችላል፡፡

h) The Chief Registrar of the Federal Supreme Court;

i) Three judges from Federal Courts elected by Federal Judges' General Meeting of which two from the three shall be female ;

j) One from Ethiopian Bar Association practicing lawying having not less than Seven years' practice;

k) One legal academican having not less than ten years of teaching experience nominated by the association or consortium of law schools of accredited higher education institutions;

l) One distinguished citizen appointed by the Council in accordance with Article 2 (15) of this Proclamation and criteria to be approved by the Council,

2/ The President and Vice President of the Federal Supreme Court shall respectively be the Chair person and Deputy Chairperson of the Council.

3/ Where the Chairperson and Deputy Chairperson are unable to carry out their responsibilities; the Council may elect one of the Council members as temporary Chairperson.

፬/ ማንኛዋም የጉባዔው አባል በጉባዔው የተወሰኑትን ደንቦች ወይም ውሳኔዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፯. **የሥራ ሚስጥር ስለመጠበቅ**

፩/ ጉባዔው በይፋ እንዲገለጹ ያላደረጋቸው የጉባኤው ውይይቶች፣ የቀረቡ ሀሳቦችና የተደረጉ ክርክሮች ይዘት ሚስጢራዊነት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም የጉባዔ አባል ወይም በጉባዔው ስብሰባዎች የሚሳተፍ ሰው ሚስጢራዊነትን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

**የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩/ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ብቃት አላቸው ብሎ ያመነባቸውን ዕጩ ዳኞች በተቻለ መጠን ከሁሉም ክልሎች መልምሎ ለሹመት ያቀርባል፤

፪/ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትነትና እና ም/ፕሬዚዳንትነቶችን ጨምሮ ለፌደራል ዳኞች በዕጩነት የሚቀርቡትን ሰዎች መልምሎ እጩዎቹን በተመለከተ ከማንኛውም ሰው እና ቦታ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ወይም እንዲሰበሰብ በማድረግ ብቁ የሆኑትን ለሹመት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በማቅረብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያደርጋል።

4/ Members of the Council shall abide by all rules and decisions of the Council.

7. **Confidentiality**

1/ All deliberations not officially disclosed by the Council shall remain confidential.

2/ Any member of the Council or any person who participates in meetings of the Council has the responsibility to respect confidentiality of deliberations of the Council.

8. **Powers and Duties of the Council**

The Council shall have the following Powers and Duties;

1/ To select and nominate competent candidates as much as possible from all Regions for judgeship for Federal courts;

2/ To collect or cause to be collected all and any relevant information from any person or institution concerning candidates nominated for appointment as Federal judges, President and Vice-President of the Federal High Court and First Instance Court and nominate and present to the Prime Minster candidates who are eligible to appoint by the House of Peoples' Representatives.

፫/ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት የፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ሬጅስትራሮች፣ ረዳት ዳኞች እና ሌሎች የፍርድ ቤት የሥራ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ደመወዛቸውን፣ አበላቸውን እና ሌሎች ጥቅሞቻቸውን እንዲሁም ከሥራ የሚሰናበቱበትን ሁኔታ ይወስናል፤

፬/ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፹፩/፬/ መሠረት ከክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔዎች በሚቀርቡለት የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዕጩ ዳኞች ላይ አስተያየቱን ይሰጣል፤

፭/ የጉባዔውን ጽ/ቤት አደረጃጀትና የሚሰራበትን መመሪያ ያወጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፮/ ጉባዔው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚመሩበት የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤ ኮሚቴዎች የተመደቡባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣታቸውን ይቆጣጠራል፤ በየወቅቱም ይገመግማል፤ በግምገማው መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

፯/ በፌደራል መጀመሪያ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንቶች፣ ም/ፕሬዚዳንቶች እና የፌደራል ዳኞች ላይ የቀረበን የዲስፕሊን ክስ ይመረምራል፤

፰/ የዳኞችን እድገት፣ ደመወዝ፣ አበል፣ እረፍት፣ ሕክምና እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፤

3/ To appoint the heads of the Secretariat offices, Registrars of the Federal Courts, assistants judges and other officials of the Council upon presentation by the President and decide on their salaries, allowances, other benefits and the conditions upon which they may be removed from their positions;

4/ To forward its opinion on the list of Regional Supreme and High Court candidate judges, submitted to it by Regional Judicial Administration Councils pursuant to Article 81(4) of the Constitution;

5/ To issue work Directive for the Secretariat of the Council and supervise its implementation;

6/ To Issue working procedure of sub-committees and periodically evaluate whether committees carry out their responsibilities and make decisions accordingly;

7/ To follow up and decide on disciplinary cases instituted against presidents and vice presidents of Federal high and first instance courts and Federal judges and to follow up its implementation;

8/ To decide on the promotion, salary, allowance, leave, medical and other benefits of Federal judges;

፱/ የፌደራል ፍ/ቤት ዳኞች የሚመሩበት የሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክሶች የሚታዩበትን የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

፲/ በወንጀል የተጠረጠሩ የፌደራል ዳኞችን ያለመከሰስ መብት ያነሳል፤

፲፩/ የፌደራል ፍ/ቤቶች እጩ ዳኞች ምልመላ የሚከናወንበት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

፲፪/ ለፌደራል ፍርድ ቤት የዳኞች ምልመላና መረጣ ስራ ሙያውና ተቀራራቢ ችሎታ ያላቸውን ሴቶችን ያካተተ ስለመሆኑ ይከታተላል፤

፲፫/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና የፌደራል ዳኞች የሥራ አፈፃፀም መመዘኛ ሥርዓት ያወጣል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም በየጊዜው ያሻሽላል፤

፲፬/ ለጉባዔው አባላት የሚከፈለውን አበል ይወስናል፤

፲፭/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን ደንብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣል።

፱. <u>የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩/ የጉባዔውን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፤

፪/ ከጽ/ቤት ኃላፊው ጋር በመመካከር አጀንዳ አዘጋጅቶ ለጉባዔው ያቀርባል፤

9/ To issue a Judicial Code of Conduct and Rules of Disciplinary Procedure for Federal judges and to follow up its implementation;

10/ To remove immunity of federal judges suspected of criminal offences;

11/ To Issue detailed Directives for selection of candidates for Federal court judges;

12/ To Issue women who have a competent become mainstreamed into nomination and recruitment for Federal Courts;

13/ To issue Performance Appraisal criteria for presidents and vice presidents of Federal Courts and other Federal Judges and to follow up its implementation;

14/ To decide on the allowances to be paid for members of the Council;

15/ Issue Regulation to administer administrative workers of Federal Courts by the House of Peoples' Representatives.

**9. <u>Powers and Duties of the Chair Person of the Council</u>**

The Chairperson of the Council shall have the following Powers and Duties:

1/ To preside over the meetings of the Council;

2/ To prepare and present to the Council meeting agendas in consultation with the Council Secretariat;

፫/ በጉባዔው የተመለመሉ እጩ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን, የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶችን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለማሾም ዝርዝራቸውን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፬/ የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት በበላይነት መምራት፣ ይቆጣጠራል፡፡

## ፲. የጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ ሥልጣን ተግባር

የጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፦

፩/ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፪/ ሌሎች በሰብሳቢ ተለይተው የሚሰጡን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፩. የጉባዔው ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩/ ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪/ ከጉባዔው አባላት ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫/ በዚህ አዋጅ ጉባዔዉ በልዩ ሁኔታ ድምጽ እንዲሰጥባቸዉ የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ፤የጉባኤው አባላት በድምፅ ብልጫ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

3/ To Present to the Prime Minister candidates selected by the Council as judges to the Federal Courts, president and vice president of the Federal High Court and First Instance Court for appointment by the House of Peoples' Representatives;

4/ To direct and supervise the Secretariat of the Council.

## 10. Powers and Duties of the Deupty Chairperson of the Council

The Deputy Chairperson shall:

1/ Represent and preside over the meetings of the Council in absence of the Chairperson; and;

2/ Perform other tasks as assigned to by the Chairperson of the Council.

## 11. Meeting of the Council

1/ The Council shall hold a regular meeting once in a month; however, it may meet at any time where found necessary;

2/ There shall be a quorum where two thirds (2/3) of the members of the Council are present;

3/ Notwithstanding exceptional circumstances which require special majority, decisions of the Council shall be passed by a simple majority vote of the members present at a meeting; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote;

፬/ የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔ አባል ጉዳዩ ታይቶ እስኪያልቅ ድረስ የቀረበበትን ዲስፕሊን በሚመለከት የሚደረግ የጉባኤው ጠቅላላ ስብሰባም ሆነ በተመደበበት ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩-፬ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

**፲፪.የጉባዔው አባላትን ሥልጣን እና ኃላፊነት በውክልና መስጠት የማይቻል ስለመሆኑ**

ማንኛውም የጉባዔዉ አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባር በውክልና ለማናቸውም ተቋም ወይም ግለሰብ መስጠት አይችልም፡፡

**፲፫ ቃለ መሐላ**

የጉባዔው አባሎች የተጣለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት ባላቸው ዕውቀትና ልምድ በነጻነት፣ በገለልተኝነት፣ እና በዚህ አዋጅና በአገሪቱ ሕጎች መሰረት በአግባቡ የሚፈጽሙ ለመሆናቸው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በጉባኤው ሰብሳቢ አማካኝነት በቃለ መሐላ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**፲፬ የጉባዔው ኮሚቴዎች**

፩/ጉባዔው ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው የጉባዔውን አባላት የያዙ ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል። ሆኖም የጉባዔው አባል ያልሆኑ ሌሎች ባለሙያዎች ከጉባዔው አባላት በተጨማሪ በኮሚቴው ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ።

4/ A member of the Council against whom disciplinary proceedings are instituted shall not sit in meetings of the Council or in committee meetings in which his case is concerned;

5/ Without prejudice to the Provisions of Sub-Article 1 - 4 of this Article, the Council may draw up its own rules of procedure.

**12. Prohibition of Delegating Powers And Responsibilities of Members of the Council**

Without prejudice to this Article 6 Sub-Article (3) of this Proclamation, any member of the Council shall not delegate its Powers and responsibilities entrusted to its by this Proclamation to any individual.

**13. Oath**

Members of the Council shall, before assuming office, take an oath affirming that they will carry out the high responsibilities conferred on them to the best of their knowledge and experience fairly, independently, impartially and in accordance with the letter and spirit of the laws of the country.

**14. Committees of the Council**

1/In order to effectively carry out its responsibilities, the Council shall organize ad hoc and standing committees whose membership may be drawn from members of the Council or non-members of the council.However other standing committee members whose not a member of a council become including on the Committee.

፪/ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የሚከተሉትን ኮሚቴዎች ያደራጃል፡-

ሀ) የዕጩ ዳኞች ምልመላ፣ የዳኞች እድገት እና ዝውውር ጉዳዮች ኮሚቴ፤

ለ) የሰው ሀብት፣ የበጀት፣ የፋይናንስ፣ የደመወዝ፣ አበል እና ጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ኮሚቴ፤

ሐ)የዳኞች ሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ኮሚቴ፡፡

፫/ የጉባዔው ኮሚቴዎች ለእያንዳንዳቸው ቋሚ ባለሞያዎች ከጽ/ቤቱ ይመደብላቸዋል፡፡ ባለሙያዎቹም የኮሚቴዎቹን የቀን ተቀን ሥራ ከኮሚቴዎቹ ሰብሳቢዎች እና ከጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ይሰራሉ፤

፬/ የኮሚቴው አባላት የተመደቡበትን ኃላፊነት በማናቸውም መልክ ለሌላ የጉባዔው አባል ወይም ለሌላ ወገን በውክልና ሊሰጡ አይችሉም፤

፭/ ኮሚቴዎቹ ጉባዔው በሚያወጣው የአሰራር ደንብ መሰረት ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡

## ፲፭. ስለጉባዔው ጽ/ቤት

፩/ የጉባዔው ጽ/ቤት አንድ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ በጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፤

፪/ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ጉባዔው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት በጉባዔው ይሾማል፤

2/ Without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, the Council shall organize the following committees:-

a) Candidates selection, judge promotion and transfer, committee;

b) Human Resource, budget & finance, salary, allowances and benefits committee;

c) Judicial Code of Conduct and Discipline committee.

3/ Each committee of the Council shall have expert assigned by the Secretariat on permanent basis. The assigned expert shall carryout the day to day activities of the committees in accordance with the guidance given to them by the head of the Secretariat and chairpersons of respective committees;

4/ Committee members shall not delegate their responsibilities to other Council members or any other person;

5/ Committees shall perform their respective duties in accordance with working procedures adopted by the Council.

## 15. Secretariat of the Council

1/ The Secretariat of the Council shall have a head of Secretariat, budget and necessary staff;

2/ The Head of the Secretariat shall be appointed by the Council in accordance with criteria approved by the Council;

፫/ የጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነት ለጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፤

፬/ የጽ/ቤት ኃላፊ የጉባኤው ስብሰባዎች ፀሐፊ ይሆናል።

፲፮. <u>የጉባኤው ጽ/ቤት ተግባር እና ኃላፊነት</u>

የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የጉባዔውን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት ማዘጋጀት፤ሲፈቀድም በጀቱን ማስተዳደር፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ መሰረት በፌደራል ዳኞች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበል ለሚመለከተው ኮሚቴ መምራት፤በአቤቱታዎቹ ላይ ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላላ ጉባዔው ማቅረብ፤

፫/ በጉባዔው የተወሰኑ ውሳኔዎች በሰብሳቢው ፊርማ ለሚመለከተዉ አካል እንዲደርስ ማድረግ፤ ውሳኔዎቹ መፈጸማቸውን መከታተል፤

፬/የፌደራል ዳኞች የግል ማህደርን ማደራጀት፣ አስፈላጊ መረጃዎችም በማህደሮቹ መግባታቸውን መከታተል፣ የግል ማህደሮች በሚመለከተው ኮሚቴ ሲፈለጉ ማቅረብ፤

፭/ የጉባዔውን እና የኮሚቴዎችን የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎችን ሌሎች ሰነዶችን በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ፤

፮/ በጉባዔው በሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ውስጥ በቋሚነት የሚያገለግሉ ከኮሚቴው ኃላፊነት ጋር ተዛማጅ እውቀት እና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በቋሚነት መመደብ፤ ሥራቸውንም መከታተል፤

3/ The Head of the Secretariat shall report to the Chairperson of the Council;

4/ The Head of the Secretariat shall serve as secretary to Council meetings.

16. <u>**Powers and Duties of the Secretariat**</u>

The Secretariat shall have the following Powers and Duties:

1/ To prepare, annual work plan and budget of the Council;

2/ To receive complaints on judges presented pursuant to Article 38 of this Proclamation; refer the complaints to the relevant committee and present recommendations of the committee on such complaints to the Council;

3/ To present the decisions with the signature of the chairperson of the council to relevant body and follow up and implement the decisions;

4) To organize personal files of federal judges; follow-up that the files are updated with necessary information and present files when requested by relevant committee of the Council;

5) To organize, file and keep full and comprehensive documents on the Council's and sub-committees' minutes and other relevant records in an appropriate manner;

6) To assign permanent experts to committees who have the competence, skills and experience relating to the work of committees and follow up their performance;

፯/ ዳኞች ሙያቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣

፰/ የዳኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በፍርድ ቤቱ አስተዳደር በቋሚነት መከናወኑን ማረጋገጥ፣

፱/ የፌደራል ዳኞችን አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ከሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እና ባለሙያዎች ጋር በመሆን አፈፃፀማቸውን መከታተል፡፡

**፲፯. <u>የጉባዔው ጽ/ቤት ኃላፊ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

የጉባዔው ጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉትን ሥልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፡፡

፩/ ከጉባዔው ሰብሳቢ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የጉባዔውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከጉባዔው ሰብሳቢ ጋር በመሆን ማዘጋጀት፣ ከስብሰባው ቀን ቢያንስ ሶስት ቀናት አስቀድሞ ለጉባዔው አባላት እንዲደርስ ያደርጋል ፣

፪/ በጉባዔው ስብሰባዎች ላይ በፀሐፊነት መገኘት፣ ቃለ ጉባኤ መያዝ፣ ቃለጉባኤዎቹ በአባላቱ መፈረማቸውን ያረጋግጣል፣

፫/ የጉባዔውን ጽ/ቤት የቀን ተቀን ሥራ በኃላፊነት መምራት፣ይቆጣጠራል፣

፬/ የጉባዔውን የተለያዩ ኮሚቴዎች ቢሮ ማደራጀት፣ የኮሚቴዎቹን ባለሙያዎች እና ረዳት ሠራተኞችን ይመድባል፣

፭/ የጉባዔው አባላትን አበል በየጊዜው ይከፍላል፣

7) To Prepare various training for judges to enhance their professional skills;

8) To ensure that appraisal of federal judges is regularly conducted by the court administration in accordance with the standard issued by the Council;

9) To follow-up implementation of administrative matters regarding Federal judges together with relevant committees' chairmen and experts.

**17. <u>Powers And Duties of The Head of The Secretariat</u>**

The Head of the Secretariat of the Council shall have the following Powers and Duties:

1/ Under the guidance and supervision of the Chairperson of the Council, to prepare agendas for Council meetings and distribute to all members of the Council at least three days in advance of the meeting of the Council.

2/ To serve as secretary on meetings of the Council, keep minutes of the Council; follow up that minutes are signed by members of the Council;

3/ To Coordinate and manage the day today function of the Secretariat Office.

4/ To organize offices of the sub-committees of the Council and assign secretaries assistants for the committees.

5/ To pay allowances to members of the Council.

፯/ ከኮሚቴ ሰብሳቢዎች ጋር በመመካከር የጉባዔውን ስትራቴጃዊ እና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለጉባዔው ሰብሳቢ ያቀርባል፤

፯/ የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ማስተዳደር፤ ይቆጣጠራል፤

፰/ ስለጉባዔው ዕቅድ አፈጻጸም በጉባዔው በተጠየቀ ጊዜ በጉባኤው ሰብሳቢ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ሪፖርት ያቀርባል፤

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሙሉ መፈጸም፣ያስፈጽማል

፲/ በጉባዔው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

6/ In consultation with the chairpersons of the committees, to prepare and present the annual work plans and budgets of the Council to the Chairperson of the Council;

7/ To lead staff of the Secretariat;

8/ Under the guidance and supervision of the Chairperson of the Council, to present regular reports to the Council on the implementation of the work plan;

9/ To perform or cause to be performed all activities under Article 16 and other relevant provisions of this Proclamation;

10/ To perform other duties assigned to his by the Chairperson of the Council.

## ፲፰. ስለጉባዔው አባላት የሥራ ዘመን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩ ከፊደል ተራ ሀ፣ ለ፣ሐ፣ መ፤ ሠ እና ሰ ከተመለከቱት በስተቀር የሌሎች የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም የሥራ ጊዜውን የጨረሰ የጉባኤ አባል ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ ድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

## 18. Term of Office of Members of the Council

With the exception of members of the Council appointed under Article 1 from a - g the term of office of all other members shall be four years. A member may be re-elected only for one additional term.

## ፲፱.የጉባዔው አባሎች ሥራቸውን ስለሚለቁበት ሁኔታ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮(፩ ) ሀ፣ ለ፣ሐ፣መ፤ ሠ እና ሰ ከተመለከቱት በስተቀር ማንኛዋም የጉባኤ አባል፤

ሀ) ከደንብ መተላለፍ ውጭ በሆነ ወንጀል ተከሶ ሲፈረድበት፤

ለ)በጤና ችግር ምክንያት ስራውን በአግባቡ ማከናወን ሲሳነው፤

## 19. Removal From Membership of The Council

1. With the exception of members of the Council appointed under Article 6 (1) (a), (b), (c), (d), (e) and g, a member of the Council shall cease to be a member thereof when:
   a) He is sentenced to imprisonment for commission of a criminal offence,
   b) He becomes incapable to properly discharging his duties due to illness;

ሐ) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤት አባልነት ሲመረጥ ወይም በሹመት፣ ወይም በዝውውር በፌደራል ወይም በክልል መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ቦታ ሲመደብ፤

መ) ይህን አዋጅ ወይም የጉባዔውን የውስጥ የአሰራር ሥነ ሥርዓት ባለማክበሩ ጉዳዩ ለጉባኤው ቀርቦ ለአባልነት ተገቢ አለመሆኑ ከጉባኤው ጠቅላላ አባላት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወሰን፤

ሠ) በሌላ ማናቸውም ምክንያት በጉባኤው ላለዉ ከፍተኛ ኃላፊነት አባል ሆኖ ለመቀጠል የማይችል ሲሆን እና በጉባኤዉ ሲወሰን፤ ከጉባዔው አባልነት ይሰናበታል ፡፡

፪/ ማንኛውም የጉባኤው አባል ከጉባኤው ጽሕፈት ቤቱ በኩል ከአንድ ወር አስቀድሞ ለጉባዔው በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የዳኞች ሹመት፣ ሥልጠና፣ የሥራ ዘመንና ከኃላፊነት መነሳት

### ፳. የፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆና ለመሾም የሚያበቁ አጠቃላይ ሁኔታዎች፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩፣ ፳፪ እና ፳፫ የተደነገጉት ተጨማሪ ሁኔታዎች በቅደም ተከተል ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሚሾሙ ዳኞ ያላቸው ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፡-

c) He is elected to the House of Peoples' Representatives or appointed to or transferred to an executive position in Federal or State Government;

d) He is disqualified from membership by a two-thirds vote of the Council for violating internal Regulations and procedures of the Council;

e) He is otherwise declared unfit for the high responsibilities of the office.

2. Any member of the Council wishing to resign shall provide a one-month prior notice to the Council in writing through the Secretariat.

## CHAPTER THREE

## Judicial Appointment, Training, Tenure and Termination

### 20. General Requirements for Appointment as a Federal Judge

Without prejudice to the applicability of additional requirements under Article 21, 22, and 23 of this Proclamation on judges appointed respectively to the Federal First Instance court, Federal High Court and Federal Supreme court, a person who fulfils the following may be appointed as a Federal judge:-

፩) በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

፪) ከፍተኛ ግብረገብነት (ሞራል) ያለዉ፣ጨዋነቱ፣ ቅንነቱ፣ ሀቀኝነቱ የተረጋገጠ፤ እና ሕዝብ ከሚነቅፋቸው ሞራል ነክ ልማዶች፣ ሱሶችና አስነዋሪ ልማዶች የራቀ፤

፫) በታማኝነቱ፣ በሥራ ወዳድነቱ፣ በእውቀትና በጤንነት የተሟላ ሆኖ የዳኝነትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመሸከም ባለው ችሎታና ፈቃደኝነት ለቦታው ተገቢ የሆነ፤

፬) ከፍ ያለ የፍትህ ስሜት ያለው እና ለሕግ የበላይነት መከበር ቁርጠኛ የሆነ፤

፭) ዳኛ ሆኖ ለመስራት ሙሉ ፍቃደኛ የሆነ፤

፮) ከደንብ መተላለፍ ውጭ በወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፤

፯) ዕድሜዉ ከ፴ ዓመት ያላነሰ፤

፰) እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ ትምህርት ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ፡፡

**፳፩. <u>በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚያበቁ ተጨማሪ ሁኔታዎች፤</u>**

በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ የሚሾም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፳ ከተደነገገው በተጨማሪ የሚከተሉትን የሚያሟላት ይኖርበታል፡፡

፩/ ቢያንስ ሶስት ዓመት ረዳት ዳኛ ሆኖ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የሰራ እና በአገልግሎቱ መልካም ሥነ- ምግባርን ፣ ትጋትን ፣ ችሎታ ፣ ብቃትና ቅንነትን ያሳየ ያረጋገጠ የሚያሟላ መሆኑ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔው ሥር በተቋቋመው የዳኞች ምልመላ ኮሚቴ የተረጋገጠ፤ ወይም

1) Be an Ethiopian National;

2) Have a proven reputation for probity, integrity, honesty, and be free from morally repugnant conduct;

3) Be of good health and display a sense of duty, responsibility and diligence of the highest standard fitting the position by virtue of his competence to assume the responsibility of being a judge;

4) Have a sense of justice and is committed to respect for the rule of law;

5) Be willing to serve as a judge;

6) Be free from criminal conviction except for minor contraventions ;

7) Be not less than the age of 30;

8) Hold at least an LLB Degree from a recognized institution of higher learning.

**21. <u>Additional Requirements for Appointment as Judge at Federal First Instance Court</u>**

A persons eligible for appointment as Federal First Instance Court judge shall fulfil the following in addition to general requirements specified under Article 20 of this Proclamation.

1/ At least three years of experience as assistant judge and whose track record for sincerity, integrity, diligence and competence is ascertained by the candidates' recruitment committee of the Council;

፪/ በክልል ፍርድ ቤቶች ቢያንስ ለሶስት ዓመት በዳኝነት ያገለገለ በአገልግሎቱ መልካም ሥነ-ምግባርን፣ትጋትን፣ ችሎታ፣ ብቃትና ቅንነትን ያሳየ ያረጋገጠ እና ይህም በምልመላ ኮሚቴ የተረጋገጠ እና አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ ሥልጠና ለመውሰድ ፍቃደኛ የሆነ፤

፫/ በዐቃቤ ሕግነት ወይም የሕግ አማካሪ ወይም ጠበቃ በመሆን ቢያንስ ለሦስት ዓመት ያገለገለ፤

፬/ ነገረፈጅ በመሆን ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሕግ መምህር በመሆን ወይም በሌላ የሕግ አገልግሎት ሥራ ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ፤ በአገልግሎቱም መልካም ሥነ-ምግባርን፣ትጋትን፣ ችሎታ፣ ብቃትና ቅንነትን ያለው እና ይህም በመልማይ ኮሚቴው የተረጋገጠ፤

፭/ እጩዎቹ አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ ሥልጠና ለመውሰድ ፍቃደኛ እና ዝግጁ መሆናቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ፤

፮/ በዚህ አንቀጽ የተገለጹት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በተለያየ ሙያ እና ተቋም ያገለገሉ እጩዎች የስራ ልምድ ስሌት እና የትምህርት ዝግጅት ደረጃ ከስራ ልምድ ጋር ምጥጥን የሚከናወንበትን መመሪያ ጉባዔው ያወጣል።

**፳፪.በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚያበቁ ተጨማሪ ሁኔታዎች**

በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ የሚሾም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፳ ከተደነገገው በተጨማሪ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባታል፡፡

2/ One who has served as judge`s assistant and worked as judge in regional courts for at least three years; and whose track record for sincerity, integrity, diligence and competence is ascertained by the Judges recruitment committee of the Council,

3/ One who served as a public prosecutor or legal advisor or Lawyer for three years;

4/ Legal advisor or attorney or lecturer in law in an institution of higher learning or any other area as legal professional for five years; and whose track record for sincerity, integrity, diligence and competence is ascertained by the Judges recruitment committee of the Council,

5/ The candidates shall be willing and show readiness to participate in additional training where necessary,

6/ Notwistanding the criteria specified under this provision the Council will issue a Directive for the conduct of ratio of work experience and educational background and for the calculation of work experience of candidates who served in various profession and institution.

**22. Additional Requirements for Appointment as Judge at Federal High Court**

A persons eligible for appointment as Federal High Court judge shall fulfil the following in addition to general requirements specified under Article 20 of this Proclamation.

፩/ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዳኝነት ወይም በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ቢያንስ ሰባት ዓመት ያገለገለ እና በአገልግሎቱ፡ መልካም ሥነምግባርን ፣ ትጋትን፣ ችሎታ፣ ብቃትና ቅንነትን ያሳየ ያረጋገጠ ይህም በዳኞች ምልመላ ኮሚቴ ከተረጋገጠ፤

፪/ በዐቃቤ ሕግ ወይም የሕግ አማካሪ ወይም ጠበቃ በመሆን ቢያንስ ሰባት ዓመት ያገለገለ፤

፫/ ነገረፈጅ በመሆን ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሕግ መምህር በመሆን ወይም በሌላ የሕግ አገልግሎት ሥራ ቢያንስ አስራ ሁለት ዓመት ያገለገለ እና በአገልግሎቱ፡ መልካም ሥነ-ምግባርን፣ ትጋትን፤ ችሎታን፣ ብቃት እና ቅንነትን ያሳየ፤ ይህም በምልመላ ኮሚቴ የተረጋገጠ፤

፬/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው ቢኖርም ከተጠቀሰው የአገልግሎት ጊዜ ሶስት አራተኛውን ያገለገለ በሥራዉ ላይ በቆየበት ጊዜ መልካም ሥነ-ምግባሩ፣ ታታሪነቱ እና የላቀ ሞያዊ ብቃቱ የተመሰከረለት ሰው የጉባዔውን ሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ካገኘ በልዩ ሁኔታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኛ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፤

፭/ እጩዎቹ አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ ሥልጠና ለመውሰድ ፍቃደኛ እና ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸዉ፤

፮/ በዚህ አንቀጽ የተገለጹት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በተለያየ ሙያ እና ተቋም ያገለገሉ እጩዎች የስራ ልምድ ስሌት የሚከናወንበትን መመሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣል፡፡

1/ One who has served as a Federal First Instance court judge or One who has served as a Regional High Court judge for at least seven years and whose track record for sincerity, integrity, diligence and competence is ascertained by the candidates' recruitment committee of the Council; or

2/ One who has served a public prosecutor or attorney or legal consultant as a State High Court judge for at least seven years,

3/ one who has served as legal advisor or as lecturer in law in an institution of higher learning or any other legal service for at least twelve years and whose track record for sincerity, integrity, diligence, and competence is ascertained by the candidates' recruitment committee of the Council;

4/ Notwithstanding sub-article 'a',' b' and 'c' of this article, a person who throughout his career has demonstrated sincerity, integrity, dedication, diligence and competence of the highest standard and has served 3/4th of the prescribed period of service for each position could be nominated for appointment to the Federal High court by a two thirds majority vote of the Council;

5/ The candidates shall be willing and show readiness to participate in additional training where necessary;

6/ The Council shall issue a Directive to calculate the length of service of candidates who served at various profession and institutions.

## ፳፫. በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚያበቁ ተጨማሪ ሁኔታዎች

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፳፪ ከተደነገገው በተጨማሪ የሚከተሉት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

፩/ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ቢያንስ አስር ዓመት ወይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ቢያንስ አስር ዓመት ያገለገለ እና በሥራዉ ዘመን መልካም ሥነ-ምግባርን ፣ታታሪነትን ፣ ብቃትን እና ቅንነትን ያሳየ፤ ይህም በዳኞች ምልመላ ኮሚቴ ከተረጋገጠ፤ ወይም

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በዳኝነት ሙያ ከተጠቀሰው የአገልግሎት ጊዜ ሁለት ሶስተኛውን ያገለገለ በዳኝነት ሥራዉ ላይ በቆየችበት ጊዜ መልካም ሥነ-ምግባሩ፣ ታታሪነቱ እና የላቀ ሞያዊ ብቃቱ የተመሰከረለት ሰው የጉባዔውን ሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ካገኘ በልዩ ሁኔታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ ልትቀርብ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም የህግ ሙያ ቢያንስ ፳ ዓመት ያገለገለ በሥራው ላይ በቆየችበት ጊዜ መልካም ሥነ-ምግባሩ፣ ታታሪነቱ እና የላቀ ሞያዊ ብቃቱ የተመሰከረለት ሰው የጉባዔውን ሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ካገኘ በልዩ ሁኔታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል።

## 23. Additional Requirements for Appointment as Federal Supreme Court Judge

A persons eligible for appointment as Federal Supreme Court judge shall fulfil the following in addition to general requirements specified under Article 22 of this Proclamation.

1/ One who has served as a Federal High Court judge for at least ten years and who demonstrated dedication, sincerity, integrity and competence is ascertained by the judge's recruitment committee of the council; or

2/ Notwithstanding Sub-Article 1 of this article, a person who throughout her career has demonstrated sincerity, integrity, dedication, diligence and competence of the highest standard and has served 2/3th of the prescribed period of service for each position could be nominated for appointment to the Federal Supreme court by a two thirds majority vote of the Council.

3/ Notwithstanding Sub-article 1, and 2 of this article, a person who throughout his career has demonstrated sincerity, integrity, dedication, diligence and competence of the highest standard and has served at least 20 years of service in any legal profession could be nominated for appointment to the Federal Supreme court by a two thirds majority vote of the Council.

**፳፬. <u>በፌደራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስለሚሾም ጊዜያዊ ዳኛ</u>**

፩/ ከአንቀጽ ፳ እስከ ፳፫ ያለዉ እንደተጠበቀ ሆኖ መልካም ሥነ-ምግባሩ፣ ታታሪነቱ እና የላቀ ሞያዊ ብቃቱ የተመሰከረለት ሰው ለዳኝነት ስራዉ የላቀ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል ተብሎ የሚገመት እና ቢያንስ ፲፭ ዓመት በህግ ሙያ የሥራ ልምድ ያለውን የተወሰነ ጊዜ በዳኝነት የሰራ ሰው ጉባዔው በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ከተቀበለዉ ለተወሰነ ጊዜ በፌደራል ከፍተኛ ወይም መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚያገለግል ጊዜያዊ ዳኛ አድርጎ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያሾም ይችላል።

፪/ የጊዜአዊ ዳኛ የስራ ዘመን ከ ፫ ዓመት አይበልጥም።

፫/ በዚህ አዋጅ ስለ ፌደራል ዳኞች የተገለጹት ግዴታዎች ለጊዜያዊ ዳኛም ተግባራዊ ይሆናሉ።

፬/ የጊዜያዊ ዳኛ መብቶች እና ጥቅሞች ጉባዔዉ በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል።

**፳፭. <u>የዳኞች የሥራ ዘመን</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ዳኞች ከሥራ ስለሚሰናበቱት ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም የፌደራል ዳኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ፷፭ ዓመት ይሆናል፡፡ ፷ ዓመት ዕድሜ የሞላ ዳኛ ከፈለገ ጡረታ ሊወጣ ይችላል።

**24. <u>Adhoc Judges of Federal High court and First Instance Courts</u>**

1/Notwithstanding article 20-23 of this Proclamation, a person who has demonstrated sincerity, integrity, dedication, diligence and professional competence of the highest standard and has served at least 15 years in public office could be nominated as an ad-hoc judge by 2/3rd majority vote of the council and appointed by the House of Peoples' Representative.

2/ The term of service of an ad-hoc judge shall not be more than 3 years.

3/ An ad-hoc judge shall be subjected to all obligations of federal judges which set-forth in this Proclamation.

4/ The rights and benefits of ad-hoc judges shall be determined by the Regulation issued by the council.

**25. <u>Tenure of Judges</u>**

1/ Without prejudice to provisions under Article 31 of this Proclamation on termination, once appointed judges, enjoy full security of tenure until they reach the mandatory age of retirement, which is set at 65 (sixty-five) years. A judge may retire at 60 years of age if he wishes to do so.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ፩ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ፳፭ ዓመት በመንግስት ሥራ ያገለገለ የፌደራል ዳኛ በ፶፭ ዓመቱ ሲፈልግ ጡረታ ሊወጣ ይችላል።

፫/ ከአቅም በላይ በሆነ ህመም ምክንያት የዳኝነት ስራዉን ማከናወን ያልቻለ እንደሆነ ቢያንስ ሀያ ዓመት በፌደራል ፍርድ ቤት በዳኝነት ያገለገለ ዳኛ ጡረታ እንዲወጣ ጉባዔዉ ሊወስን ይችላል።

፬/ በዚህ ህግ ያልተሸፈኑ ከጡረታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸዉ የመንግስት ሠራተኞች የሚመለከቱ የጡረታ ሕጎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

## ፳፮. የዳኞች የደረጃ እድገት እና ዝውውር

፩/ አንድ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ ተሹሞ ባለበት ፍርድ ቤት የደረጃ ዕድገት የሚያገኘዉ በሥራው ላይ ባሳየው ግልጽብቃት ፣ ትጋት ፣ አገልግሎት እና መልካም ሥነ-ምግባር ላይ ብቻ ተመስርቶ በሚቀርብ ምክረ ሀሳብ መሠረት በጉባዔው ሲወሰን ነው፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

፪/ ጉባዔዉ አስፈላጊ ሲሆንና በቂ ምክንያት ሲኖር ዳኛ በፍቃደኝነት ከአንድ የፌደራል ፍርድ ቤት ደረጃ ወደ ሌላ የፍርድ ቤት ደረጃ በጊዜያዊነት መድቦ ሊያሰራ ይችላል፡፡

2/ Without prejudice to Sub-Article 1 of this provision, a Federal judge who works in public service for 25 years may retire at the age of 55 .

3/ The council may allow a judge who serves 20 years as a judge if he encounters suffers from serious illness which affects his judicial work.

4/ Relevant civil servants' pension laws shall be applicable for all pension related issues which are not covered by this Proclamation.

## 26. Promotion and Transfer of Judges

1/ A Federal judge shall be promoted within the same level of court based on demonstrated competence, dedication, diligence and service and upon recommendations submitted to and accepted by the Council.

2/ The council may temporarily assign a Federal Judge on his will from one level of Federal Court to another when necessary and for good cause.

፫/ ዳኛ ከችሎት ወደ ችሎት ወይም ከምድብ ችሎት ወደ ምድብ ችሎት ለማዘዋወር ልዩ ሞያዊ ክህሎትን ፣ ብቃትን ፣ ልምድን እና የዝውውሩን አስፈላጊነት መሰረት በማድረግ ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር በየደረጃው ባሉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች አማካኝነት ይሆናል፡፡የቅሬታ አፈታት እና አቀራረብ በሚመለከት ዝርዝሩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

## ፳፯. የዳኞች ሥልጠና

ዳኞች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚዘጋጀው ሥልጠና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ፳፰. ስለዳኞች ደመወዝ

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ሌሎች የፌደራል ዳኞች ደመወዝ የኑሮ ሁኔታን እና የሀገሪቱን የኢኮኖሚ አቅም መሰረት በማድረግ እንደአግባብነቱ በጉባዔው ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## ፳፱. የዳኞች ጥቅማ ጥቅሞች

፩/ አግባብነት ያላቸዉ የዳኞችን መብቶች እና ጥቅሞች የሚደነግጉ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በስራ ላይ ያለ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ የቪ.አይ. ፒ አገልግሎት ያገኛሉ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳኞች ጥቅማጥቅም ዝርዝር ጉዳይ በሚመለከት ጉባኤው ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

3/ Any judge may be transferred from one division to another or from one place to another place by the decision of the respective presidents of Federal courts taking in to account the professional competence and experience of the judge and the necessity of the situation that makes the transfer necessary. Details including complaint handling procedures shall be specified by a Directive to be issued by the Federal Supreme Court.

## 27. Training of Judges

Judges shall have the duty to undergo in all regular and continuing judicial trainings.

## 28. Salary of Judges

The salary of the president and vice president of the Federal Supreme Court and all other Federal judges may be determined by the Council take into account the living standard and economical capacity of the country.

## 29. Benefits of Judges

1/ Without prejudice to relevant laws related to judges' rights and benefits, a judge of Federal courts shall have nd VIP service.

2/ Without prejudice to the detail regarding rights and benefits of judges may be determined by a Regulation issued by the council.

**፴. የዳኞች እረፍት እና በጥናትና ምርምር ሥራ መሳተፍ**

፩/ ዳኞች የወሊድ፣አባትነት፣ የአክል እና ሌሎች እረፍቶች ይኖራቸዋል። ዝርዝሩ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፪/ የዳኝነት ሥራቸውን በማይቃረን መልኩ የፌደራል ዳኞች በሥልጠና እና ምርምር የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

፫/ ያልተቋረጠ ከአስር ዓመት ያላነሰ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም የፌደራል ዳኛ ጥናት ወይም ምርምር ለማድረግ ጉባዔው በሚያወጣው መስፈርት እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፴፩. የዳኞች የሥራ ስንብት**

፩/ ማንኛውም የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፡፡

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ በተመለከተው የጡረታ መውጫ እድሜ ሲደርስ ወይም ዳኛው ፷ አመት ሞልቶት በጡረታ መሰናበት ሲፈልግ፤

ለ.ከዳኝነት ሥራ ለመልቀቅ ጥያቄ ሲያቀርብ የሁለት ወር ቅድሚያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

**30. Leave of Federal Judges Participation in Research**

1/ Federal Judges shall have annual, maternity, paternity, accident and other leaves which shall be determined by a Regulation issued by the council.

2/ Federal judge shall have the right to participate in research and training consistent with their judicial function.

3/ A Federal judge who has completed uninterrupted service of at least 10 years shall have the right to up to 6 months research leave necessary for research undertakings. Details shall be specified in a Directive to be issued by the Federal Supreme Court.

**31. Termination of Tenure**

1/ The tenure of any Federal court judge shall not be terminated except on the following grounds:

a) When attains a retirement age as indicated under Article 25 of this Proclamation or where he has attained age 60 and wishes to retire;

b) where tenders resignation by giving a three months advance written notice;

ሐ. ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ ሲታይ እና ይህም በጉባዔው ተረጋግጦ ከዳኝነት ሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤

መ. የዳኝነት ስራውን በአግባቡ ለማከናወን የማያስችል ህመም ሲያጋጥመዉ፤

ሠ. የሥነ-ምግባር ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ እና ይህም በጉባዔው ሲረጋገጥ እና ከዳኝነት ሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) እና (ሠ) በተመለከቱት ሁኔታዎች ዳኛ ከሥራ እንዲሰናበት ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ነዉ።

**፴፪.ከስራ ስለተሰናበተ ዳኛ ክልከላዎች**

፩/ ስለጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ የሚደነግጉ ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሥራዉ የተሰናበተ የፌደራል ዳኛ ሥራው ካቆመበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት አስቀድሞ ይሰራበት በነበረው የፌደራል ፍርድ ቤት ደረጃ በሚገኝ ማናቸውም ችሎት ፊት በጠበቃነት ተከራካሪዎችን ወክሎ መቅረብ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ስራ የለቀቀ የፌደራል ዳኛ በጥብቅና ስራ በመሰማራቱ ለፌደራል ዳኞች አግባብነት ባለዉ ህግ የተፈቀዱ ጥቅማጥቅሞችን ከማግኘት አያግደዉም።

c) Serious illness which bars a judge from properly undertake his judicial service;

d) where manifests gross incompetence, and this is ascertained by the Judicial Administration Council and a decision is made to end her tenure;

e) Where committed a breach of discipline and ascertained by the Judicial Administration Council and a decision is made to remove .

2/ A decision made by the Council to remove the judge under Sub-Article 1 (c) and (e) of this article shall be effective where the House of Peoples' Representatives approves the decisions of the Council.

**32. Prohibitions of Termination of Tenure**

1/ Without prejudice to other laws regarding licensing of attorneys, a federal judge whose tenure is terminated shall not appear before any bench at federal court level in which he served as a judge representing litigants for a period of two ears starting from the last date of termination of office.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this article engagement of a former federal judge in attorney service shall not be a cause to lose benefits prescribed under other relevant laws.

፫/ በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራው የተሰናበተ የፌደራል ዳኛ ከሥራ ስንብት ጋር በተያያዘ ለፌደራል ዳኞች በሕግ የተፈቀዱ ከጡረታ ውጭ ያሉ ጥቅማጥቅሞችን አያገኝም፡፡

**፴፫. <u>የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከሥራ ስለመሰናበት</u>**

፩/በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩(፩)(ሀ)(ለ)(መ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፴፩(፩)(ሐ)(ሠ) በሚመለከት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት ነው።

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ስለቀረበበት ክስራ የሚሰናበቱት ጉዳይ ጉባዔው ታይቶ ውሳኔ ሲያገኝ እና ጥያቄው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት ለህዝብ ተወካዮች ቀርቦ ምክርቤቱ ውሳኔውን በአብላጫ ድምጽ ሲያጸድቀው ነው ፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>
## <u>የዳኞች መብት</u>

**፴፬. <u>ያለመከሰስ መብት</u>**

፩/ የፌደራል ዳኞች በሰጡት ውሳኔ ምክንያት በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም የፌደራል ዳኛ በከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ ወይም በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ያለመከሰስ መብቱ ካልተነሳ በስተቀር ሊትያዝ ወይም ሊታሰር እና ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

3/ A Federal judge whose tenure is terminated on grounds of breach of discipline shall not be entitled to receive benefits payable by law upon termination of tenure of judges.

**33. <u>Termination of Tenure of President and vice President of Federal supreme ourt</u>**

1/ Without prejudice to article 31(1) (a)(b)(d) of this proclamation, article 31(1)(c) or (e) shall be applicable to the President or vice President of the Federal Supreme Court pursuant to the following procedures;it shall be applicable on the basis of this article Article Sub (2).

2/ The case concerning the termination of tenure president or vice president shall be decided by the Council and following the request of the Prime minster the House Peoples Representatives shall approve the decision by simple majority vote.

## <u>CHAPTER FOUR</u>
## <u>Rights of Judges</u>

**34. <u>Judicial Immunity</u>**

1/ Federal judges may not have civil liability for actions taken in their official capacity.

2/ A Federal judge may not be arrested, detained or prosecuted unless caught grave crime in flagrante delicto his immunity is lifted by the Council.

፫/ ዳኞች ያለመከሰስ መብት የሚነሳበት ስነ-ሥርዓት ጉባዔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

**፴፭. የመናገር እና የመፃፍ ነፃነት**

የዳኝነትን ነጻነት እና ገለልተኝነት መርሆችን እና በዳኞች የዲስፕሊን ደንብ የሚቃረን እስካልሆነ ድረስ ዳኞች በሕገ መንግሥቱ እና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች በተረጋገጠው መሠረት የመናገር፣ የመፃፍ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተሳትፎ የማድረግ፣ መብት አላቸው፡፡

**፴፮. የፓለቲካ ፓርቲ አባል ስላለመሆን እና ፓለቲካዊ ተሳትፎ**

፩/ በየትኛውም ደረጃ ባለ የፌደራል ፍርድ ቤት የተሾመ ዳኛ የማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን፤ ወይም የፖለቲካ እንቅስቃሴ አራማጅ ወይም ደጋፊ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ስብሰባዎች ላይ ተሳታፊ መሆን አትችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞች የመምረጥ መብት አላቸው፡፡

፫/ ማንኛውም የፌደራል ዳኛ የፖለቲካ ፓርቲን ወክሎ ወይም በግል በምርጫ ለመወዳደር የፈለገ እንደሆነ ምርጫው ከሚካሄድበት ቀን አንድ ዓመት ቀድሞ የዳኝነት ሥራውን መልቀቅ አለበት፡፡

3/ The detail procedure of lifting of judges 'immunity shall be determined by the Regulation issued by the federal supreme court.

**35. Freedom of Expression**

Federal Judges shall have the right to speak, write, participate in social and religious affairs, participate in training and research undertakings as provided for and guaranteed under the Constitution and other laws provided this may not be inconsistent with the principles of judicial independence and impartiality.

**36. Prohibition against Membership in a Political Party and Political Participation**

1/ No Federal judge shall be a member of any political party or advance active political causes publicly or be a supporter of same or participate in political party meetings.

2/ Without prejudice to Provisions under Sub-Article (1) of this Article, judges shall have the right to elect.

3/ A judge who wishes to run for political office may do so provided he resigned judicial post at least one year in advance of the Election.

## ምዕራፍ አምስት

## ስለዳኝነት ነጻነት፣ ግልጽነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነት

**፴፯.የዳኝነት ሥራን በግልጽ ፣ በገለልተኝነት እና በተጠያቂነት መንፈስ ስለማከናወን**

፩/ በፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ማናቸውም ፍርድ፣ ብይን፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ ከማንኛውም የውስጥም ሆነ የውጭ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ በሕግና ፍሬ ነገር ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

፪/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኗቸው የዳኝነት ሥራ ተግባራት ለሕዝብ ግልጽ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ በችሎት የሚደረጉ የዳኝነት ክንውኖች ለተከራካሪ ወገኖች ፣ ለሕዝብ እና ለመገናኛ ብዙሐን ክፍት ሆነው ለማስተናገድ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ዝርዝሩን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ ፍርድ ቤቶች ማናቸውንም ተከራካሪ ወገኖች ያለ አድልኦ በእኩልነት የማስተናገድና በተለይ በወንጀል ተከሰው በጥበቃ ሥር ሆነው ጉዳያቸው በመታየት ላይ ያሉ ሰዎችን አያያዝ ሁኔታ የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**፴፰. ስለ ዳኛ ኃላፊነት**

፩/ ማንኛውም የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ በያዘው ጉዳይ ላይ ግልጽ፣ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

## CHAPTER FIVE

## JUDICIAL TRANSPARENCY, IMPARTIALITY AND ACCOUNTABILITY

**37. Conducting Judicial Activities with Transparency, Imparitality and Accountablilty**

1/ Decision, order and ruling of federal court shall solely be based on the facts and the law and shall be free from any internal or external interference.

2/ The judicial activities of Federal courts shall be transparent and public. Unless provided otherwise by law, they shall conduct judicial proceedings in an open court.

3/ Judicial proceedings of any Federal court shall be made in ways that allow access to the public and the media. Details shall be provided by a Directive to be issued by the Federal Supreme Court.

4/ Federal courts shall have the duty to treat all parties with impartiality and equality. They shall in particular follow up the condition of detention of individuals held in custody accused of criminal offences pending trial.

**38. Responsibility Of A Judge**

1/ Every Federal Judge shall have the duty to be transparent, free and impartial on cases assigned.

፪/ በተለየ ሁኔታ በሕግ ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም የፌደራል ዳኛ የዳኝነት ጉዳዮችን በግልጽ ችሎት የማየት ግዴታ አለበት፡፡

፫/ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የፌደራል ዳኛ በዳኝነት ሥራው ላይ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ወይም በሕግ አግባብ መፈጸም ያለበትን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ በዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬/ አግባብነት ባለው ሕግ ካልተወሰነ ወይም ጉባዔው ካልወሰነ በስተቀር ማንኛውም የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ በዳኝነት ሥራው ላይ እያለ በሕግ አውጭው ወይም በአስፈጻሚው አካል ሥራ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ተመድቦ ሊሰራ አይችልም፡፡

## ፴፱. <u>በሥነ-ምግባር ጥሰት ክስ ስለማቅረብ</u>

፩/ በዳኝነት ሥራ አካሄድ ላይ ግልጽ የሆነ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ማንኛውም ሰው ወይም ስለ መፈጸሙ ማስረጃ ያለው ለዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ አቤቱታ፣ ወይም ጥቆማ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በተፈጸመ የዳኝነት ሥነ ምግባር ጥሰት ምክንያት በዳኛው ላይ የዲስፕሊን ክስ የቀረበ እንደሆነ ክሱ በፍጥነት መታየትና መወሰን ያለበት ሆኖ ዳኛው የሚቀርብበትን ክስ የማወቅና የመከላከል መብት አለው፡፡ ዝርዝሩ በዳኞች ሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ Unless decided otherwise in accordance with law, every federal judge shall have the duty to hold proceedings of cases assigned in public.

3/ Every Federal judge shall be accountable for breach of judicial code of conduct where he commits an offence on account of his judicial duties as a judge or fails to do what is required to do.

4/ Unless determined by relevant law or decided by the council, any Federal judge shall not assume responsibility or be assigned to work either permanently or temporarily to any function relating to the work of the legislative or executive organ while serving as a judge.

## 39. <u>Complaint on Judicial Misconduct</u>

1/ Any person who is of the belief that a judge acted in violation of the judicial Code of Conduct or any one with evidence on such violation may submit a petition, complaint or provide information to the Council,

2/ Where, because of the alleged violation the judge is charged for, the proceedings shall be speedy and the judge who is the subject of the proceedings shall have the right to know and defend herself against the charges. Details shall be provided in the Judicial Code of Conduct and Rules of Disciplinary procedure.

፫/ በዳኛ ላይ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት አቤቱታ ያቀረበ ሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የማወቅ መብት አለው፤

፬/ በሥነ-ምግባር ጥሰት ምክንያት በቀረበ ክስ በዳኛ ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ በሕገ መንግስቱ፣ በዚህ አዋጅና በሥነ ምግባር ደንቡ መሰረት ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵. የጉባዔዉ የበጀት አስተዳደር ነፃነት

የጉባዔውንና የጽ/ቤቱን ሥራ በአግባቡ ለማስፈፀም የሚያስችል በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይመደብለታል፡፡

### ፵፩. ኦዲት

የጉባዔዉ የሒሳብ አያያዝና የበጀት አጠቃቀም በፌደራል ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

### ፵፪. የሰው ሀብት

፩/ ጉባዔው የራሱን ሠራተኞች የመመልመል፣ የመቅጠርና የማስተዳደር ነፃነት አለዉ፡፡

፪/ጉባዔው እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ ፣ ቅጥር ፣ ምደባ ፣ እድገት ፣ ዝውውር ፣ ሥልጠና ፣ የሥልጠና ፣ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ እና የጉባኤዉ ሠራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ የሚወስነው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማስፈጸም በሕዝብ ተወካዮች ምክር በሚወጣው ደንብ ነው፡፡

3/ The person who brought complaints against the judge shall have the right to know the decisions on the case.

4/ Any disciplinary action taken against the judge shall solely be based on the Constitution, this Proclamation and the Judicial Code of Conduct and Disciplinary Rules of Procedure.

## CHAPTER SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 40. Budgetary Allocation

Federal Judicial Administration council shall allocate its budget by the House of peoples' Representatives which shall be sufficient to properly administer the office.

### 41. Audit

The books of accounts and budget of the council shall be audited annually by the Federal Auditor General.

### 42. Human Resources

1/ The Council shall have independence to recruit, hire and administer their own non-judicial personnel.

2/The recruitment, hire, placement, promotion, transfer, training, salary increments and benefits and disciplinary matters of administrative personnel of Federal courts shall be governed by a Regulation adopted by the House of Peoples Representatives.

## ፵፫. ቃለ መሐላ

በማናቸውም ደረጃ የሚሾም ፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በሕገመንግስቱ መሰረት ቃለ መሐላ ይፈፅማል፡፡ የቃለ መሐላውም ይዘት የሚከተለው ይሆናል፡፡

"እኔ----------- የፌደራል -----------ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኜ ስሾም አንዱን ከሌላው ሳላበላልጥ ከማንኛውም ወገንተኝነት ነጻ ሆኘ የኢ.ፌ.ድ.ሪን ሕገ መንግስት እና የኢትዮጵያ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ፍትሕን ለማስፈን እና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር በፍፁም ነፃነት፣ገለልተኝነት እና ከፍተኛ ትጋት ሀገሬን እና ሕዝቡን ለማገልገል ቃል እገባለሁኝ"፡፡

## ፵፬. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ደንቦችን ያወጣል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን አዋጅ እና ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፵፭. የተሻሩ ሕጎች

፩/ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፬/፪ሺ፪ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ ሕግ፤ ደንብ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከተ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 43. Oath

A Federal judge appointed at any level shall before assuming responsibilities take oath in accordance with the constitution.

."I -------as a Federal --------court -------- judge do swear that I will administer justice and protect rule of law with absolute impartiality, independence and diligence only based on the constitution and Ethiopian laws and free from any bias".

## 44. Power to Issue Regulation

1/ The Judicial Administration Council shall issue the necessary Regulations to give effect to this Proclamation.

2/ The Federal Supreme Court may issue Directives for the implementation of this Proclamation.

## 45. Repealed laws

1/ The Federal Judicial Administration Council Establishment Proclamation No. 684/2010 is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

2/ No other Law or Customary practice which is inconsistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters provided for in this Proclamation.

**፵፮ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት ተጀምረው የነበሩ በዳኞች ላይ የቀረቡ የዲሲፕሊን ክሶች በዚህ አዋጅ በተቋቋመው ጉባዔ ታይተው ይወሰናሉ፡፡

፪/ የአስተዳደር ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ እስከሚወጣ ድረስ የሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ እድገትና አስተዳደር የዚህን አዋጅ መርሆዎች ሳይቃረን ቀድሞ ሲሰራበት በነበረው ሕግ መሰረት ይቀጥላል፡፡

**፵፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ከጥር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፫ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

**46. Transitional Provisions**

1/ Pending disciplinary cases brought against judges shall be decided by the Council established by this Proclamation .

2/ Recruitment, placement, promotion and transfer of non-judicial personnel after the coming in to force of this Proclamation shall be governed in accordance with previously applicable law without contravening the principles provided for in this Proclamation until the issuance of the Regulation regarding the administration of non-judicial personnel.

**47. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of its approval by the House of Peoples' Representatives on the $21^{st}$ day of January 2021.

**Done at Addis Ababa, On this $20^{th}$ Day of May, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**